# የመንፈስ ቅዱስ ትምህርት መግቢያ

- ***የመንፈስ ቅዱስ መለኮትነት***

*መንፈስ ቅዱስ መለኮትነት ባህርይ አለው?*
*መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ ጋር እኩል የሚመለክና የሚሰገድለት አምላክ ነው። እግዚአብሔር ብቻ ሊኖረው የሚገባው ባህርይ በሙሉ መንፈስ ቅዱስም አለው። ስለዚህ እንደ ሀይል ብቻ መቁጠር ስህተት ነው ፣በመጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ተብሎ ተጠርቷል።*
*ሐዋ*5፣3-4

| መለኮታዊ ባህርይ | አብ | ወልድ | መ/ቅዱስ |
|---|---|---|---|
| ዘላለማዊ | መዝ 90፡2 | ራእይ 1፡7-8 | ዕብ 9፡14 |
| በሁሉም ስፍራ የሚገኝ | ኤር 23፡24 | ማቴ 18፡20 | መዝ 139፡7 |
| ሁሉን አዋቂ | ኤር 17፡10 | ራዕይ 2፡23 | ዮሐ 14፡26 |
| ሁሉን ቻይ | 1 ጴጥ 1፣3 | 2 ቆሮ 12፣9 | ኢዮብ 33፡4 |
| | | | |

- እብ 9፡14
በ-------------------------------ራሱን ለእግዚአብሔር ያቀረበ የክርስቶስ ደም እንዴት ይልቅ ህያውን እግዚአብሔርን ልታመልኩ ከሞተ ስራ ህሊናችሁን ያነጻ ይሆን?
- መዝ 139፡7
ከ---------------------------ወዴት እሄዳለሁ ከፊትህስ ወዴት እሸሻለሁ?
- ዮሐ 14፡26
አብ በስሜ የሚልከው ግን ------------------------------- የሆነው አጽናኝ እርሱ------------ያስተምራችኋል።
- ኢዮብ 33፡4
-----------------------------------------ፈጠረኝ -------------------------------- የአምላክ እስትንፋስ ህይወትን ሰጠኝ።

- ***የመንፈስ ቅዱስ ህልውና***

*መንፈስ ቅዱስ ህልውና አለው?*
*አንድን ነገር ህልውና አለው ለማለት ሶስት ነገሮች መሟላት ይኖርባቸዋል።*
*ይኸውም* 1-*ዕውቀት* ፣2- *ስሜትና* 3-*ፈቃድ ናቸው።*
*ሰው ህልውና ስላለው በእውቀቱ ያውቃል፣ በስሜቱ ይጠላል፣ ይወዳል፣ በፈቃዱ ደግሞ ይወስናል፣እሺ ወይንም፣ እምቢ ይላል።*

- ***መንፈስ ቅዱስ ዕውቀት አለው***

1ቆሮ 2፡10-11 በእርሱ ውስጥ ካለው መንፈስ በቀር ለሰው ያለውን የሚያውቅ ሰው ማነው? እንዲሁም ደግሞ --- ----------------------------------- በቀር ለእግዚአብሔር ያለውን ------------------------------------------------.

- ***መንፈስ ቅዱስ ስሜት አለው***

*ይወዳል፣ ይጠላል፣ ይደሰታል፣ ያዝናል…*

ኤፌ 4፡30
ለቤዛ ቀን የታተማችሁበትን ____________ _______________ ______________.
ኢሳ 63፡10-------------------

- ***መንፈስ ቅዱስ ፈቃድ አለው***

ይመራል ሮሜ 8፡14 ፣ ይልካል ሃዋ 13፡4 ፣ ይከለክላል ሀዋ 13፡6
ይልካል ሃዋ 13፡4 እነርሱም ------------------------- ------------------------ ወደ ሴሌውቅያ ወረዱ.....

## ***የመንፈስ ቅዱስ ስራ***

- ***አለምን የመውቀስ አገልግሎት***

ዮሐ 16፡8-11
እርሱም መጥቶ ስለ ------------------------ ስለ ----------------------ስለ ----------------------- አለምን ይወቅሳል።

- ***ዳግም ልደትን የመስጠት አገልግሎት***

ቲቶ 3፣5

*ነገር ግን የመድሀኒታችን የእግዚአብሔር ቸርነትና ሰውን መውደዱ በተገለጠ ጊዜ እንደምህረቱ መጠን ---------------------------በሚሆነው መታጠብና ------------------------- --------------------አዳነን።*

ዮሐ 3፡5-6

- *ኢየሱስም መልሶ እውነት እውነት እልሀለሁ ሰው ከውሀና -----------------ካልተወለደ በቀር ወደእግዚአብሔር መንግስት ሊገባ አይችልም ከስጋ የተወለደ ---------------ነው ከ-------------------------የተወለደ ---------------------- ነው;*

- ***ባማኝ ውስጥ የመኖር አገልግሎት***

ዮሀ 14፡ 15-17

*እኔም አብን እለምናለሁ ---------------------- ከናንተ ጋር እንዲኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል እርሱም ዓለም የማያየውና የማያውቀው ስለሆነ ሊቀበለው የማይቻለው የዕውነት መንፈስ ነው ነገር ግን ከ ------------------------- ስለሚኖር-------------------- ስለሚሆን ታውቃላችሁ።*

- ***የማጥመቅ አገልግሎት***

1. ***በአካል ውስጥ መጠመቅ***

*አጥማቂው-መንፈስ ቅዱስ*
*አላማው-ለአዲስ መንፈሳዊ ህይወት*
*ውጤቱ-የመንፈስ ፍሬ*
1ኛ ቆሮ 12፡13
*አይሁድ ብንሆን የግሪክ ሰዎች ብንሆን ባሪያዎችም ብንሆን ጨዋዎችም ብንሆን እኛ ሁላችን----------------------- -----------------------------------------------------------*

2. ***በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ***

*-.አጥማቂው- ኢየሱስ*
*አላማው- ለምስክርነት ሀይልን ለማግኘት*
*ውጤቱ*
*የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ*
ማር1፡ 8
*እኔ በውሀ አጠመቅኋችሁ ---------------- ግን ----------------------ያጠምቃችኋል እያለ ይሰብክ ነበር።*
ሐዋ 1፡5
*ዮሀንስ በውሀ አጥምቆ ነበርና እናንተ ግን ከጥቂት ቀን በኋላ --------------------------- -------------------- አለ።*

- ***የማተም አገልግሎት***

ኤፌ 1፡13

*እናንተ ደግሞ የዕውነትን ቃል ይኸውም የመዳናችሁን ወንጌል ሰምታችሁ ደግሞም በክርስቶስ አምናችሁ --------------------------------- ------------------------ ------------------------- እርሱም------------------------------- ነው።*

- ***የመሙላት አገልግሎት***

ኤፌ 5፡18

*መንፈስ ------------------------- እንጂ በወይን ጠጅ አትስከሩ ይህ ማባከን ነውና።* ሐዋ 4፡31፣ ሐዋ 7፡55

## የመንፈስ ቅዱስ ትምህርት
## ጥናት 1
## መንፈስ ቅዱስን እንተዋወቀው

**መግቢያ**

የማናውቀውን አዲስ ሰው ባንድ ጊዜ መግባባት ቀላል አይደለም። በመሀል አንድ የሚያስተዋውቅ ሰው ሲኖር ግን ቀለል ይላል። በዚህ ክፍል ጌታ ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱ ብዙ የማያውቁትን መንፈስ ቅዱስን ሲያስተዋውቃቸው እንመለከተዋለን።

**ዓላማ**

መንፈስ ቅዱስ ጌታ ኢየሱስ ከሄደ በኋላ ወደምድር በመምጣት በሚያምኑት እና በማያምኑ ሰዎች ህይወት ውስጥ የሚያከናውነውን አገልግሎት መግለጽ ነው።

**የንባብ ክፍል፡**

ዮሐንስ 16፡5- 15

**የቡድን ውይይት**

- ስለመንፈስ ቅዱስ በምታስብበት ጊዜ ወደ አይምሮህ የሚመጣው ምን ድነው?

በዮሐንስ 13-17 ጌታ ኢየሱስ ወደመስቀል ከመሄዱ በፊት ያሉትን የመጨረሻ ማሳሰቢያዎቹን እናያለን። እርሱ ወደ አባቱ እንደሚሄድና እነርሱ ከርሱ ጋር መሄድ እንደማይችሉ ይነግራቸዋል።

1. ጌታ ይህን ሲነግራቸው የደቀ መዛሙርቱ ስሜት ምን አይነት የሚሆን ይመስልሀል? ለምን?
   ቁ7 እኔ ግን ዕውነት እነግራችኋለሁ--------- ------------------- ----------------------------------
   እኔ ባልሄድ አጽናኙ ወደ እናንተ አይመጣም --------------- ----------- ----------- ---------- ----------- -----------------------

2. ለምን ይመስልሀል ጌታ ኢየሱስ መንፈስ ቅዱስን አጽንኝ ብሎ የጠራው?
   ቁ7 እኔ ባልሄድ ---------------------- ወደ እናንተ አይመጣምና

3. በምን መንገድ ነው የጌታ ወደ አባቱ መሄድና የመንፈስ ቅዱስ መምጣት ሊጠቅማቸው የሚችለው?
   ቁ7 እኔ ባልሄድ ---------------------- ወደ እናንተ አይመጣምና እኔ ብሄድ ግን ------- ---------------- -------------------------

4. ከቁ 8-11 መንፈስ ቅዱስ ለዓለም ያለውን አገልግሎት ጌታ ኢየሱሰ ገልጸታል; ከዚህ ቃል በመነሳት የማያምኑ ሰዎች የክርስቶስ ወንጌልን በሚሰሙ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ በምን በምን ነገሮች ነው የሚወቅሳቸው?
   ቁ8 እርሱም መጥቶ --------------------------- -------------------- -------------------------------
   - ዓለምን ይወቅሳል፡ መውቀስ ሲባል ምን ማለቱ ነው ብለህ ታስባለህ?

በቁ 10-11ላይ
ስለ ሀጢያት --------------------------------------------------------
ስለጽድቅም --------------------------------------------------------
ስለፍርድም -------------------------------------------------------

- -ይህን በቁጥር 10-11 ላይ ያለውን ሀሳብ ትርጓሜ አስረዳ።

5. በቁጥር 12 እና 13 መሰረት የመንፈስ ቅዱስ ለአማኞች አገልግሎት ምን ሆኖ ታየዋለህ?

   ቁ 12 የምነግራችሁ ገና ብዙ አለኝ ነገር ግን አሁን ልትሸከሙት አትችሉም። ግን እርሱ የዕውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ---------------------------------------- ------------------------------

- እንጂ ከራሱ አይነግርምና ------------------------ ----------------------

6. ከቀ 14-15 ባለው ቃል መሰረት መንፈስ ቅዱስ ከኢየሱስ ጋር ስላለው ህብረት ምን መረዳት ታገኛለህ?
   ቁ 14 እርሱ------------------------------------------
   ----------------------------------------------------------------ይነግራችኋል

ምዕራፍ 15፡26ን አንብብና ተጨማሪ ከየሱስ ጋር ያለውን ግንኙነት ተናገር
ቁ 26 ዳሩ ግን እኔ ከአብ ዘንድ -------------------------- አጽናኝ እርሱም ከአብ የሚወጣ የዕውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ እርሱ-------------------------------------------------- .እናንተም ደግሞ ከመጀመሪያው ከእኔ ጋር ኖራችኋልና ------------------------------.

<u>ማዛመድ</u>

- ለአማኞች የሆኑ የመንፈስ ቅዱሰ አገልግሎቶች እስካሁን ባየነው ክፍል ውስጥ ተገልጸዋል እነርሱም፣ <u>ማጽናናት</u>፣ _ <u>መምራት</u>፣ <u>መናገር</u>፣ <u>ኢየሱስን ማክበር</u>፣ <u>ስለኢየሱስ መመስከር</u> ባሁኑ ጊዜ ላንተ በጣም የሚያስፈልግህ አገልግሎት የትኛው ነው ብለህ ታስባለህ ? ለምን?

- ዛሬ ከተማርከው ትምህርት ስለመንፈስ ቅዱስ ምን አዲስ ግንዛቤ አገኘህ? ታዲያ ምንስ ለምድረግ ታስባለህ?

## የመንፈስ ቅዱስ ትምህርት
## ጥናት 2
## የመንፈስ ቅዱስን መውረድ

**መግቢያ**

እግዚአብሔር አንድ ነገር ሲያደርግ ያን የሚገልጽበት ሀይለኛ መንገድ አለው። በብሉይ ኪዳን ህዝቡን ከባርነት ሲታደግ በታላቅ ክንድና ታምራት አወጣቸው። የላከው ልጁ ስለሰው ሀጢያት ሞቶ በተቀበረ ጊዜ በታላቅ ሀይል መቃብር ፈንቅሎ ከሞት አስነሳው። እነዚያን ጥቂት ደቀመዛሙርት አበረታትቶ ለወንጌል ተልዕኮ ለማውጣት ደግሞ ሌላ ግሩም ሀይሉን ላከ፣ ያም መንፈስ ቅዱስ በሀይል በበዓለ ሀምሳ ቀን የወረደበት ሁኔታ ነው።

**ዓላማ**

ለወንጌል ተልዕኮ ሀይልን ለመልበስ የመንፈስ ቅዱስ መውረድ አስፈላጊ መሆኑን ለማየት።

**የንባብ ክፍል፡**

**የቡድን ውይይት**

መንፈስ ቅዱስ ከጥንት ጀምሮ በዓለም ነበር። ግን በበዓለ ሀምሳ ቀን በአዲስ ሀይልና አሰራር ለመጀመሪያ ጊዜ ወረደ።አማኞች በአዲስ ብርታትና በአዲስ ተልዕኮ ተሞሉ።
ሐዋ 2፡1-13

1. ከቁጥር 1-4 በበዓለ ሀምሳ ቀን ብትኖር እና ሁኔታውን በቪዲዮ ቀርጸህ ብታስቀር ኖሮ የትኛውን ክንዋኔ ነበር ቀርጸህ የምታስቀረው?

2. ለተፈጠረው ነገር የተሰበሰበው ህዝብ ምላሽ ምን ነበር?

    - ይህን ሁኔታ አንተስ አይተህ ቢሆን ኖሮ ምን ትል ነበር?

3. ሐዋ 2፤14-41 አንብብና
   መንፈስ ቅዱስ ሲወርድ ለነበረው ሁኔታ ጴጥሮስ የሰጠው መግለጫ ምን ይመስል እንደነበር ተናገር።

4. ጴጥሮስ ከጠቀሰው ከኢዩ 2፡28-29 እግዚአብሄር በህዝቡ ላይ መንፈሱን ሲያፈስ ምን ይከናወናል ብለህ ታስባለህ?

5. ከቁጥር 22-36 በዚያ የነበሩት ስለኢየሱስ አገልግሎት፣ ስላደረገው ታምራት፣ ስለመሞቱ ያውቃሉ። በጴጥሮስ መልዕክት ውስጥ አዲስ የነበረው ነገር ምን ነበር?
    - ቁ 33 የመንፈስ ቅዱስ መውረድ መንስዔ ምን ነበር?

6. በቁ38 ስታነብ ጴጥሮስ ለሰዎቹ ንስሀ ቢገቡና በየሱስ ቢያምኑ ምን እንደሚሆንላቸው ነበር ያረጋገጠላቸው?

7. ከቁ 42-47 አንብበህ መንፈስ ቅዱስ ከመጣ በሁዋላ የቀደሙት አማኞች ይለማመዱት የነበረውን ኑሮና አገልግሎት ማብራራት ትችላለህ?

**ማዛመድ**

- ከላይ ከተመለከትናቸው የቀደሙት ቤተክርስቲያን ልምምዶች ባንተ ቤተክርስቲያን የትኛው ልምምድ የተዘነጋ ይመስልሀል?

- እነዚህን የቀደሙ ክርስቲያኖች በትጋት ይለማመዷቸው የነበሩትን ልምምዶች በቤተክርስቲያናችን እንዲበዛ እንዴት ለመንፈስ ቅዱስ ክፍት መሆን አለብን ብለህ ታስባለህ?

**የመንፈስ ቅዱስ ትምህርት**
**ጥናት 3**
**የመንፈስ ቅዱስ መውረድ በሐዋርያት ስራ ውስጥ ።**

**መግቢያ**

በሐዋ ምዕራፍ ሁለት ለመጀመርያ ጊዜ በታላቅ ሀይል ከወረደ በኋላ ሌሎች በግልና በህብረት ለመጀመርያ መንፈስ ቅዱስ የወረደባቸው ሰዎች ነበሩ። መንፈስ ቅዱስ አንድ አይነት ፎርሙላ አልነበረውም ግን በሁሉም ላይ ግን ለአንድ ዐላማ የወረደ መሆኑን ይኼ ጥናት ያሳያል።

**ዓላማ**

የመንፈስ ቅዱስን ሀይል መልበስ ለአማኞች ሁልጊዜም አስፈላጊ እንደሆነ መመልከት።

**የንባብ ክፍል፥**

ሐዋ 8፡14-19፣ ሐዋ 9፡10-18፣ ሐዋ 10፡ 44-48፤ ሐዋ 19፡ 1-7

**የቡድን ውይይት**

መንፈስ ቅዱስ መቀበል ሲባል ወደ አይምሮህ የሚመጣው ምንድነው?

**ሐዋ 8፡14-19**
**የሰማርያ ሰዎች**

- እነዚህ ሰዎች አማኞች ይመስሉሀል? ለምን?

ቁ 14 በየሩሳሌም የነበሩት ሐዋርያት የሰማርያ ሰዎች_______________________________ሰምተው ጴጥሮስንና ዮሐንስን ሰደዱላቸው።

- ጴጥሮስና ዮሐንስ ወደነርሱ ለምን ተላኩ? ማንስ ነው የላካቸው?

ቁ 15 እነርሱም በወረዱ ጊዜ ________________________________ ዘንድ __________________

- እነዚህ ሰዎች በምን ሁኔታ መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ?

ቁ 16-17 በጌታ በየሱስ ስም ብቻ ተጠምቀው ነበር እንጂ____________________ ___________________________________________። በዚያን ጊዜ __________________________________ __________________________________.

- ስምኦን ምን ስለተመለከተ ነው መንፈስ ቅዱስ ማደልን በገንዘብ ለመግዛት የጠየቀው?

________________________________________________________________________

**ሐዋ 9፡10-18**
**የደማስቆው ሳውል**

- ጌታ ሳውልን የት ነው የተገናኘው? በዚህ ጊዜ የዳነ ይመስልሀል?

- ሐናንያ ወደጴጥሮስ የመጣበትን ምክንያት ሲናገር ምን አለ?

ቁ 17 ሐናንያ ወደ ቤቱ ገባ ___________________________ ወንድሜ ሳውል ሆይ ጌታ እርሱም በመጣህበት መንገድ የታየህ ______________________ ነው። ደግሞም ___________________ እና _________________________ ዘንድ ላከኝ።

- ሳውል መንፈስ ቅዱስን በምን አይነት ሁኔታ ተሞላ?
- ቁ 18 ወዲያውም እንደ ቅርፊት ያለ __________________________ ያን ጊዜ ደግሞ አየ ።

**ሐዋ 10፡ 24-48**
**<u>ቆርኔሌዎስና ቤተሰቡ</u>**

- ቆርኔሌዎስ የዳነ ሰው ነበር ብለህ ታስባለህ?

ጴጥሮስ ወደ ቆርኔሌዎስ ቤት እንዴት ሊመጣ ቻለ? ከቁ 9- 23 ድረስ አንብበው።
ቁ 19 ጴጥሮስ ስለ ራዕዩ ሲያወጣ ሲያወርድ ሳለ ______________
እነሆ________________________________________
___________________________________ አለው።

- የቆርኔሌዎስ ቤተሰቦች በምን አይነት ሁኔታ መንፈስ ቅዱስ ተሞሉ?

ቁ 44 ጴጥሮስም ይህን ገና ሲናገር ________________________________ ላይ
____________________________.

- መንፈስ ቅዱስ በተሞሉ ጊዜ ከተገረዙት ወገን የሆኑት ምን አስገረማቸው?

ቁ 45 ከጴጥሮስ ጋር የመጡት ሁሉ ከተገረዙት ወገን የሆኑት ምዕመናን _____________________
ደግሞ _______________________________________ተገረሙ።
_______________________________________ ሰምተዋቸዋልና።

- ጴጥሮስ ስለዚህ ሲመሰክር በም11፡15 ላይ ምን ብሎ መሰከረ?

!!፡15 ለመናገርም በጀመርኩ ጊዜ ___________________________________
____________________________________________________________
። የሐንስ በውሀ አጠመቀ እናንተ ግን ______________________________
ያለው የጌታ ቃል ትዝ አለኝ።

**ሐዋ 19፡ 1-7**
**<u>የኤፌሶን ደቀ መዛሙርት</u>**

- እነዚህ ሰዎች ደህንነትን በተመለከተ ምን አይነት ሁኔታ ላይ ያሉ ይመስልሀል?

ጳውሎስ የጠየቃቸውን ጥያቄ እንዴት ትረዳዋለህ?

ሐዋ 19፡ 1-7 አንዳንድ ደቀመዛሙርትንም አገኘ __________________________
___________________________አላቸው።

- በምን አይነትስ ሁኔታ መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ?

ቁ 6 ጳውሎስም _______________________________________________ ጊዜ
___________________________________________________________

- ምን አይነት የጸጋ ስጦታዎችስ ተገለጡባቸው?

ቁ 6 ጳውሎስም እጁን በጫነባቸው ጊዜ ____________________________________________
_________________________:______________________________________________።

**<u>ማዛመድ</u>**
በምን መንገድ ነው በዚህ ዘመን መንፈስ ቅዱስን ልንቀበል የምንችለው ብለህ ታስባለህ?

# የመንፈስ ቅዱስ ትምህርት
## ጥናት 4
## የመንፈስ ቅዱስ ሀይል ያለብሳል ።

**መግቢያ**

እነዚያ በፍርሀት ውስጥ የነበሩ ደቀመዛሙርት ከጌታ ትንሳኤ በሁዋላ ለቀጣዩ አገልግሎታቸው ሀይል ሳይለብሱ ከኢየሩሳሌም መውጣት እንደማይገባቸው ጌታ ነግሮአቸዋል፣ እነርሱም ያን የመንፈስ ቅዱስ ሀይል በጸሎት ለ10 ቀናት ሲጠባበቁ ቆይተው ሀይል ከለበሱ በሁዋላ ታሪካቸውና አገልግሎታቸው ተለወጠ። የጌታን ወንጌል ይዘው ዋጋ እየከፈሉ እስከ ዓለም ዳርቻ ተሰማሩ።

**ዓላማ**

ወንጌልን ለመመስከር፣ በወንጌል ዕውነት ለመቆም፣ ቅድስናን ለመልበስ፣ ምስክርነትንና አገልግሎትን በተዓምራት ለማጽናት መንፈስ ቅዱስ ሀይል የሚሞላ መሆኑን ማሳወቅ።

**የንባብ ክፍል፤**

ሐዋ 1፡ 4-8 ፣ ሐዋ 4፡23-31 ፣ ሐዋ 6፡1-7 7፤54-60

**የቡድን ውይይት**

መንፈሳዊ ህይወትህ የደከመ ወይም የቀዘቀዘ ሆኖ ሲሰማህ በጸሎት ወደ ጌታ ፊት ስትቀርብ መንፈስ ቅዱስ በላይህ ወርዶ ልዩ ሀይል ሰጥቶህ ያውቃል?

**ሐዋ 1፡4-8**

1. **ለምን ይመስልሀል ጌታ ደቀመዛሙርቱን ከኢየሩሳሌም እንዳይወጡ ያዘዛቸው?**

በሐዋ 1፤4 ከእነርሱም ጋር አብሮ ሳለ ________________ _________________ አዘዛቸው፣

2. **መንፈስ ቅዱስ በወረደባችሁ ጊዜ ምን ትቀበላላችሁ ነው ያላቸው?**
**መንፈስ ቅዱስ በመቀበላቸው ምክንያት ምን ለውጦች በህይወታቸው በባህርያቸው እንዲሁም ባገልግሎታቸው ተከናውኗል? አንዳንዶቹን ጥቀስ።**

ቁ 4 ነገር ግን __________________________ ________________________

______________________________

3. **ከቁጥር 8 ሀይል የመልበሳቸው ዓላማ ምን መሆኑን ታያለህ?**

ሐዋ 1፤8 ነገር ግን________________________ ____________________________
____________________ በኢየሩሳሌም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከምድር ዳርም ድረስ______________________ ትሆናላችሁ።

**ሐዋ 4፡7 23-31**

4. **ታሪኩን አንብበህ የደቀ መዛሙርቱ የጸሎት ርዕስ ምን መሆኑን ተናገር።**

______________________________________________________________

5. **በጸለዩ ጊዜ ምን ሆነ?**

ቁ 31 ከጸለዩም በሁዋላ ተሰብስበው የነበሩበት ስፍራ ተናወጠ ____________________________ ____________________________________________ የእግዚአብሄርንም ቃል በግልጥ ተናገሩ።

6. **በዚህ ስፍራ መንፈስ ቅዱስ በሀይል በላያቸው ላይ የወረደበት ምክንያት ምን ድነው ብለህ ታስባለህ? ከ31 -37 አንብብና ምን ውጤትስ እንደ ነበረው ጻፍ?**________________________________________________________________
____________________________________________________________

<u>ሐዋ 6፡ 1-15 7፡ 54-60</u>

7. **ቁ 1-6 ሐዋርያት እስጢፋኖስ ለአገልግሎት የመረጡት ሐዋርያት በውስጡ ምነ ተመልክተው ነበር ? እንደ አገልጋይ እኛ ከዚህ ምን እንማራለን?**
______________________________________________________________________

8. **ለአገልግሎት ከተመረጠ በሁዋላ በመንፈስ ቅዱስ ሀይል ምን ያደርግ ነበር?**

ቁ 8እስጢፋኖስ ________________________________ ____________________________________________ ያደርግ ነበር።

9. **ምልክትና ድንቅ ለወንጌል ምን በር ይከፍታል ብለህ ታስባለህ?**
________________________________________________________

10. **መንፈስ ቅዱስ ተከራካሪዎቹን ለመቋቋም እንዴት ረዳው?**

ቁ 10 አንዳንዶቹ ተነስተው እስጢፋኖስን ይከራከሩት ነበር ይናገርበት የነበረውንም___________________________________________________________።

11. **ሐዋ 7፡ 54-60 የስጢፋኖስ የመጨረሻ ፍርድ በድንጋይ ተወግሮ መሞት ነበር ። መንፈስ ቅዱስ በዚያ አስጨናቂ ሁኔታ ውስጥ እንዴት ረዳው?**

ቁ 54 ይህን በሰሙ ጊዜ በጣም ተቆጡ ጥርሳቸውንም አፋጩበት፣ ____________________________________ ወደ ሰማይ ትኩር ብሎ ሲመለከት የእግዚአብሄርን ክብር ኢየሱስንም በእግዚአብሄር ቀኝ ቆሞ አየ…

12. **ያለአግባቡ ሲከሰስ እስጢፋኖስ ከወሰደው ርምጃ የምንማረው ምንድ ነው?**

ቁ 60 ተንበርክኮም ጌታ ሆይ ________________________________________ ብሎ በታላቅ ድምጽ ጮኸ።

13. **በእስጢፋኖስ መስዋዕትነት ምን ፍሬ ተገኝቷል ብለህ ታስባለህ?**
______________________________________________________________

<u>**ማዛመድ**</u> በዚህ ዘመን አማኞች የመንፈስ ቅዱስን ሀይል ለብሰው እንዳገለገሉት እንደቀደሙት አማኞች ዓይነት ህይወት ይታይባቸዋል?
ካለልሆነስ ያን ሀይል ለብሶ በሀይል ለማገልገል ምን ማድረግ አለብን ትላለህ?
_______________________________________________________________

# የመንፈስ ቅዱስ ትምህርት

## ጥናት 5

## የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች ።

**መግቢያ**

ዳግም በተወለደ ሰው ሁሉ ውስጥ መንፈስ ቅዱስ ይኖራል(ዮሐ 3፤6) ። አማኙ ፈቃዱን ለመንፈስ ቅዱስ ባስገዛ መጠን እና የጌታን መስቀል በመሸከም በመንፈስ ለመመላለስ በወሰነ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ በአማኙ ህይወት ብዙ ስራዎችን መስራት ይጀምራል። መንፈስ ቅዱስ በአማኝ ህይወት ውሰጥ ከሚሰራቸው ስራዎች መካከል ሁለት አበይት ስራዎችን እንመለከታለን፤ እነዚህም የመንፈስ ቅዱስ ፍሬና፣ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ሲሆኑ፣ በዛሬው ጥናት የምናየው የመንፈስ ፍሬዎችን ነው።

**ዓላማ**

የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች እግዚአብሄር ደስ የተሰኘባቸው የክርስቶስ ባህርያት ናቸው። እነዚህንም ባህርያት እኛ ጌታን የምንመስል ለመሆን የምናፈራቸው፣ ሌሎች ደግሞ በፍሬዎቹ የሚባረኩባቸው መሆኑን ማሳወቅ ነው።

**የንባብ ክፍል፡** ገላትያ 5፡13- 26

**የቡድን ውይይት**

በሰዎች ህይወት ውስጥ የመንፈስን ፍሬ የተመለከትክበት ጊዜ ነበርን ? ምን ተሰማህ? የስጋ ስራስ ተገልጾ ያየህበት ጊዜ አለ? ያኔስ ምን ተሰማህ?

1. **ዕውነተኛ ክርስቲያን በክርስቶስ ነጻ ወጥቷል። በዚህ ክፍል መሰረት ነጻነታችን ገደብ አለው ወይ?**

ቁ 13ወንድሞች ሆይ እናንተ ለአርነት ተጠርታችሁዋል ብቻ አርነታችሁ ---------------------------- ------------------------------ ነገር ግን -------------- -------------------------- ----------------------------

2. **የሀጢያተኛው ባህርይህና የመንፈስ ትግል በውስጥህ ተሰምቶህ ያውቃል ወይ?**

-------------------------------- ---------------------------------------- ይመኛልና ። እነዚህም እርስ በርሳቸው ይቀዋወማሉ፤ ስለዚህም ----------------------------------------------------------------------

3. **ከቁ 19-21 የተገለጡትን የስጋ ስራዎች ዘርዝራቸው**

ቁ 19-21 የስጋ ስራም የተገለጠ ነው እርሱም ------------------------------------------------------------- ----------------------------------------------------------------------------------------------------------- -------------------------------------ይህንም የሚመስል ነው።

4. **ቁ 21 ላይ ጳውሎስ እንደነዚህ ያሉትን የሚያደርጉ የእግዚአብሔርን መንግስት አይወርሱም ሲል ምን ማለቱ ነው?**
5. **የመንፈስ ፍሬዎችን ዘርዝራቸውና እንዴት በአማኝ ህይወት ውስጥ እንደሚገለጡ አስረዳ?**
6. **አሮጌውን ስጋ ከምኞቱና ከመሻቱ ጋር ከሰቀልነው ታዲያ ለምን በውስጣችን ትግል እንሰማለን?**

ቁ 24 የክርስቶስም የሆኑት ----------------------------------------------------------------------------------

7. **በመንፈስ ብንኖር በመንፈስ ደግሞ እንመላለሰ ማለት ምን ማለት ነው?**

**ማዛመድ**

- ከዘረዘርካቸው የመንፈስ ፍሬዎች በህይወትህ የቶቹ ይታያሉ የትኞቹስ ይጎድሉሀል?
- እነዚህን ባህርያት በህይወትህ ለማየት ምን ማድረግ ይገባኛል ብለህ ታስባለህ?

<u>የመንፈስ ቅዱስ ትምህርት</u>
<u>ጥናት 6</u>
<u>የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች።</u>

**<u>መግቢያ</u>**

የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ጉዳይ በብዙ አማኞች መካከል ክርክርን የሚፈጥር ሆኗል።በአንዳንድ ህብረቶች ውስጥ በስጦታው ላይ ብቻ ትኩረት ሲደረግ፣ በሌሎች ዘንድ ደግሞ ለመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ብዙ ክብደት ሲሰጠው እንመለከታለን። መጽሐፍ ቅዱስ ግን ሚዛናዊ በሆነ ሁኔታ ሁለቱም እንደሚያስፈልጉ ያሳያል ።የአንድ አማኝ ህይወት ክርስቶስን ወደመምሰል ሙላት ለመድረስ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬና የመንፈስ ቅዱስ የጸጋ ስጦታዎች ያስፈልጉታል።1ቆሮ 12 ን አንብብ።

**<u>ዓላማ</u>**

መንፈስ ቅዱስ ለአማኝ የጸጋ ስጦታዎችን ሲያድል ሌሎችን ለማነጽ እንዲገለገሉበት መሆኑን ማስረዳት።

**<u>የንባብ ክፍል፡</u>** 1 ቆሮ 12፡ 1- 11

**<u>የቡድን ውይይት</u>** የጸጋ ስጦታ ሲባል ምን ማለት ይመስልሀል? የተፈጥሮ ችሎታና የጸጋ ስጦታ ይለያያሉን?

1. **ጳውሎስ መንፈሳዊ ነገር ብሎ የሚናገረው ስለምንድነው? ስለ መንፈሳዊ ነገር ( ስጦታዎች) ማወቅ ለምን ይጠቅማል?**

   ቁ1 ስለ________________________ ወንድሞቼ ሆይ ታውቁ ዘንድ እወዳለሁ።

2. **ከቁጥር 4-6 ባለው ክፍል ላይ የሚገልጠው መሰረታዊ ሀሳብ ምንድነው?**

   ቁ 4-6 __________________ ልዩ ልዩ ነው ________________ አንድ ነው
   _____________________ ልዩ ልዩ ነው ________________ አንድ ነው
   ________________________ልዩ ልዩ ነው______________________-
   ____________________________አንድ ነው

3. **በቁጥር 7 ላይ መንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን ለምን ዓላማ ነው የሚሰጠው? ሀሳብህን አብራራው**

   ቁ 7 ነገር ግን መንፈስ ቅዱስን መግለጥ ለእያንዳንዱ________________ ይሰጠዋል።

4. **በቁጥር 8-10 ብዙ የጸጋ ስጦታዎችን ይዘረዝራል፣ ምሳሌ በመስጠት እነዚህ ስጦታዎች እንዴት እንደሚገለጹና እንደሚሰሩ ግለጽ**

   ቁ 8-10 ለአንዱ ____________________ በመንፈስ ይሰጠዋል ለአንዱም በዚያው
   መንፈስ___________________ ይሰጠዋል፣ለአንዱም በዚያው
   መንፈስ___________________ ለአንዱም በአንዱ መንፈስ______________
   ______________ ለአንዱም_______________________ ለአንዱም ___________
   _________________ለአንዱም ______________________ ለአንዱም________
   ____________________ ________

5. **እነዚህን ስጦታዎች እንዴት መቀበል ይቻላል? በኛ ፍላጎት ነው ወይንስ መንፈስ ቅዱስ እንደፈቀደ የሚያካፍላቸው ናቸው? 1 ቆሮ 14፡ 1 ን እንዴት ከዚህ ጋር እናገናዝበዋለን?**

ቁ 11 ያ አንዱ መንፈስ ____________________________________________
______________________ ያደርጋል።

6. እነዚህን ሁሉ ስጦታዎች ዛሬ በቤተ ክርስቲያን መጠቀም ይቻላል ወይ?

ማዛመድ

- በአንተ ቤተ ክርስቲያን ከነዚህ ስጦታዎች በየቶቹ ተገልግለሀል?
- የአንተስ ስጦታና ጥንካሬ በየትኛው አገልግሎት መስክ ነው? ይህንንስ ስጦታህን ሌሎች እንዲባረኩበት በምን ዓይነት መንገድ ተጠቀምክበት?
- በ1 ቆሮ 14፥1 መሰረት በብርቱ የምትፈልገው ና የምትጸልይበት የጸጋ ስጦታ አለን?

## የመንፈስ ቅዱስ ትምህርት
## ጥናት 7
## በመንፈስ ቅዱስ መገዛት ።

**መግቢያ**፤ መንፈስ ቅዱስ መሞላትንና በወይን ጠጅ መስከርን ጳውሎስ ለምን እንዳወዳደረው ራሱ በዚህ ክፍል ባይገልጽም፣ አንድ ግን የተረጋገጠ ተመሳሳይነት አላቸው:: ይሄውም ወይን ጠጅ ወይም መጠጥ የሰውን ሥጋዊ ባሕርይና ጠባይ የሚገፋፋና ሥጋዊ ሥራዎችን (ለምሳሌ ስድብ፣ ጠብ፣ ዝሙት ወዘተ) እንዲያደርግ የሚያነሳሳ እንደሆነ ሁሉ፣ መንፈስ ቅዱስም መንፈሳዊውንና መልካሙን ነገር ሰው እንዲያደርግ የሚያነሳሳ፣ የሚያነቃቃና የሚያበረታታ ነው::

**ዓላማ**፤ አማኝ በየጊዜው ህይወቱ በመንፈስ ቅዱስ የተሞላና እንዲሁም በመንፈስ ቁጥጥር መሆን እንደሚገባው ማሳወቅ።

**የቡድን ውይይት፡** በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ሰው እንዴት ይመላለሳል? እንዴትስ ይታወቃል?

**የንባብ ክፍል**፤ ኤፌሶን 5፡15፤26

1. **በቁ 15 ጥበበኞች ሁኑ የሚለው ምን አይነት ጥበብን ነው?**
   ቁ 15 እንግዲህ እንደ ______________ እንጂ ጥበብ እንደሌላቸው ሳይሆን እንዴት እንድትመላለሱ በጥንቃቄ ተጠበቁ።

2. **ጳውሎስ በቁ 16 ቀኖቹ ክፉዎች ናቸው ይላል በዚህ ትስማማለህ ወይ? ዘመንን መዋጀት ማለትስ ምን ማለት ነው?**
   ቁ 16 ________________________ ናቸውና ዘመኑን ዋጁ

3. **የጌታን ፈቃድ ዘመንን ከመዋጀት ጋር እንዴት ይያያዛል?**
   ቁ 17 ስለዚህ ________________________________እንጂ ሞኞች አትሁኑ።

4. **በወይን ጠጅ አትስከሩ ( በአልኮል ቁጥጥር ስር አትሁኑ) የሚለውን ሀሳብና በመንፈስ ተሞሉ የሚለው አባባል ንፅፅር ስለመንፈስ ቅዱስ ምን እንድትረዳ ያደርግሃል?**
   ቁ18 ________________________ እንጂ በወይን ጠጅ አትስከሩ።

5. በዚህ ጥቅስ መሰረት ሰው በመንፈስ ቅዱስ (ቁጥጥር ስር ለመሆን) ለመሞላት ምን ማድረግ **አለበት ብለህ ታስባለህ?**
6. **በቁጥር 19-20 መሰረት በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ስር በምትሆንበት ወቅት ከጌታ ጋር ያለህ ግንኙነት እንዴት አይነት ይሆናል?**

7. **በቁጥር 21 እንዳችን ለሌላው ስለመታዘዝና መሰጠት ይናገራል። ይህ ትዕዛዝ ቀደም ካለው ክፍል ጋር እንዴት ይያያዛል?**

ቁ 21 ለእያንዳንዳችሁ________________________________________________።

**ማዛመድ፡**

- በመንፈስ ቅዱስ ለተሞላ ህይወት ጥሩ ምሳሌ ሊሆን የሚችል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ወይንም በአካል የምታውቀው ሰው ካለ ስለዚያ ሰው ለምን እንደመረጥክ አስረዳ።

- አንተስ ምን ያህል በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ህይወት እየኖርክ ነው? መልስህ አይደለም ከሆነስ ምን አይነት ዕርምጃ መውሰድ የሚገባህ ይመስልሃል?